# ተው ሥማ ያገር ሰው።

ምን እየተሠራን ምን እየሆን ነው፤
ወገን ባገር ጉዳይ ዝምታው ምንድነው፤
ፕሮፌሥር ዶክተር ኢንጅነር ተማሪ፤
ወጣት ሽማግሌ የደብር ሐላፊ፤
ምን እየተሠራን ምን እየሆን ነው፤
ወገን ባገር ጉዳይ ዝምታው ምንድነው፤
ዓለም ሣይሠለጥን ሣያውቅ እራሡን
ያለች የነበረች ሐገራችንን
እያስደፈርናት ነው ክብር ሞገሷን
ስማኝ አንተ ትውልድ ሐገርህን አጥፊ
ባኩሪ ታሪክህ ላይ ድሪቶ ደራቢ
ገና ይከተላል ምኑን አየህና
ሣታውቅ እንደ አዋቂ ሁሉንም ሆንክና
በርን ከፍቶ ሠጥቶ ለጠላት ገመና
ይኸው አስቆጠርከን የህይወት ፈተና
እኳንም ያላዩ አያት ቅድመ አያቶች
አበሻና ውሻ ተብሎ ሲጠራ ለዛውም ባረቦች
ምን ይል ነበር ቴዎድሮስ ይህን ጉድ ቢሠማ
ያበሻ ልጅ አንገት በአረቦች ተቀልቶ ሜዳ ላይ ሢተኛ
ዘመን ያሣለፈች በነፃነት ኩርታ
ለትንሽ ለትልቅ ፍፁም ሣትረታ
ዛሬ ተዋረደች
ፕሮፌሰር ዶክተር ኢንጅነር አፍርታ።
ከታሪክ ተጠያቂነት ሊያድነን
የሚችል ፅናት ይስጠን።
አሜን።
ዘሪሁን ግዛው